የሐረሪ ሕዝብ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት

ሐረር ነጋሪ ጋዜጣ

HARAR NEGARI GAZETA

OF THE HARARI PEOPLE NATIONAL REGIONAL STATE

8ኛ ዓመት ቁጥር 9 8th year No 9		ሐረር መጋቢት 1/1996 HARAR 11th March 2004
ያንዱ ዋጋ Unit price 1.00	በሐረሪ ሕዝብ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ	የፖስታ ሣጥን ቁጥር P.O.Box 272

ማውጫ

አዋጅ ቁጥር 40/1996 ዓ.ም

የሐረሪ ሕዝብ ብሔራዊ ከልላዊ መንግስት የፀፐታ ምክር ቤት ማቋቋሚያ አዋጅ----------ገጽ327

አዋጅ ቁጥር 40/1996

የሐረሪ ሕዝብ ብሔራዊ ከልላዊ መንግሥት ፀፐታ ም/ቤት ለማቋቋም የወጣ አዋጅ

በሐረሪ ሕዝብ ብሔራዊ ከልል አስከአሁን ሊያጋጥሙ የነበሩ የፀፐታ ችግሮችን ለመፍታት የክልሉ መንግሥት ከፈደራል ፀፐታ ጋደሁ-ች ጋር ሊያደርገዉ የነበረዉ እንቅስቃሴ ስተጋቢ ቢሆንም ቅንጅታዊ አሠራሩ አስተማማኝ ባልሆነ የታወቀመመሪያና ወጥነት በሊሰጡ መልኩ ሁኒታዎች ሲከሰቱ ብቻ የሚያገስገል መሆኑን በመገንዘብ፣

ሲሠራበት የቆየዉን አካሄድ ችገሮችን በተገቢዉ ሁኒታ ለመፍታት በሚያስችል ቋሚና በህገ በተደገፈ የፀፐታ አደረጃጀት በክልልና በተዋረድ አስክ ቀበሌ ድረስ በማደራጀት የፀፐታን ጉዳይ የሚከታተልና አቅድ የሚያቀናጅ አካል ማቋቋም አስፈላጊ በመሆኑ፣

በሐረሪ ሕዝብ ብሔራዊ ከከልላዊ መንግሥት ሕገ መንግሥት አንቀጽ 26/2/ረ/ መሠረት የሚከተለዉ ተዉጿል፡፡

ክፍል አንድ

ጠቅላላ

1. አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ « የሐረሪ ሕዝብ ብሔራዊ ከልላዊ መንግሥት የፀፐታ ምክር ቤት ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 40/1996» ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠዉ ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ ዉስጥ፣

1. «ክልል» ማለት በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ-መንግስት አንቀጽ 47 ንዑስ አንቀጽ (1)(9) ላይ የተመለከተው የሐረሪ ሕዝብ ክልል ነዉ
2. «ሥራ አስፈፃሚ» ማለት በክልሉ ህገ መንግሥት መሠረት የተቋቋመዉ የክልሉ ከፍተኛ የህገ አስፈጻሚ አካል ነዉ፡፡
3. ምክር ቤት ማለት በዚህ አዋጅ አንቀጽ 3 መሠረት የተቋቋመዉ የክልሉ መንግሥት የፀፐታ ምክር ቤት ነዉ

ክፍል ሁለት

የፀፐታ ምክር ቤት ስለ ማቋቋም

3/ መቋቋም

የፀፐታ ጉዳይ የሚከታተል፣አቅድ የሚያቀናጅ እና የሚመራ የሐረሪ ሕዝብ ክልል ፀፐታ ምክር ቤት በርዕሰ መስተዳደሩ ጽህፈት ቤት ሥር የህገ ሰዉነት ያለዉ የክልሉ መንግስት አካል ሆኖ በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል፡፡

4/ ዓላማ

የፀፐታዉ ምክር ቤት ዓላማ በክልሉ የሚያጋጥሙና ሊያጋጥሙ የሚችሉ የፀፐታ ችግሮችን የክልሉ መንግሥትና የፈደራል የፀፐታ ሃይሎ-ች ተደራጅተዉ

በጋራ ለመፍታት የሚያስችል አደረጃጀትና አሠራር እንዲፈጠር በማድረግ የክልሉ ደህንነትና ፀጥታ መከበሩን ማረጋገጥ ይሆናል፡፡

ክፍል ሦስት

የፀጥታዉ ምክር ቤት አደረጃጀት

5. የፀጥታዉ ምክር ቤት አቋም

የፀጥታዉ ምክር ቤት:

1. የፀጥታዉ ምክር ቤት አመራርና አባላት
2. በተዋረድ የሚቋቋሙ የፀጥታ ምክር ቤቶች እና አስፈላጊ የሆኑ ሠራተኞች ይኖሩታል፡፡

6/ የፀጥታዉ ም/ቤት አመራርና አባላት

የፀጥታዉ ምክር ቤት የሚከተሉት ቅንጅታዊ አካላት ይኖሩታል፡

1. የክልሉ ርዕሰ መስተዳድር----------ሰብሳቢ
2. የክልሉ ፍትህና ፀጥታ ዘርፍ ኃላፊ-----ም/ሰብሳቢ
3. የክልሉ ፖሊስ ኮሚሽነር ----------ፀሐፊ
4. የሕረር ከተማ ማዘጋጃ ቤት ሹም-------አባል
5. የክልሉ ሚሊሻ ጉዳይ ጽ/ቤት ኃላፊ--አባል
6. የፈደራል ፖሊስ /በክልሉ የተመደበ/ኃላፊ---አባል
7. የደህንነት የክልሉ ተወካይ ----------አባል
8. የመከላከያ /በክልሉ ካሉት/ ከፍተኛ የሠራዊት አዛዥ---------- አባል

7/ ተጠሪነት

1. የፀጥታዉ ምክር ቤት ተጠሪነቱ ለሥራ አስፈጻሚ ይሆናል
2. የክልሉ ፀጥታ ምክር ቤት አባላት ተጠሪነት ለርእሰ መስተዳድሩ ይሆናል
3. የክልሉ ፀጥታ ምክር ቤት አባላት በገልና በወል የፀጥታዉን ምክር ቤት ሥር ይመራሉ ያስተባብራሉ፡፡

8/ ተግባርና ኃላፊነት

የክልሉ ፀጥታ ምክር ቤት የሚከተሉትተግባራትና ኃላፊነቶች ይኖሩታል፡፡

1. በክልሉ ዉስጥ ለፀጥታ ችግር መነሾ የሆኑና ሊሆኑ የሚችሉትን ችግሮች በዝርዝር በመገምገምና በመተንተን መፍትሄ ያስቀምጣል፡

   ለተግባራዊነቱ የቅንጅት እቅድ በማዉጣት በገልጽ የሥራ ክርናል ይገቀሳቀሳል፡

2. የክልሉን የፀጥታ ሁኔታ በሚመለከት የመረጃ ልዉዉጥ ያደርጋል፡ ከሁሉም አካላት የሚገኝ ዉን መረጃ ለፀጥታዉ አጠባበቅ መነሻ በማድረግ የፀጥታ ጥበቃ እቅድ በማዉጣት ተግባራዊ ያደርጋል፡

3. በክልሉ ዉስጥ ያሉ ለአደጋ ተጋላጭ የሆኑና ጥበቃ የሚያስፈልጋቸዉ ተቋማት በቂና የተስተካከለ ጥበቃ ያሳቸዉ መሆኑን ያረጋግጣል፡

4. የህዝቡን የፀጥታ ሥነ አእምሮ ለማጸበር የሚያስፈልጉ ሥራዎችንና በየሆቱሉና በገል ተቋማት የተቀጠሩ የጥበቃ ሠራተኞችን የማሰልጠን ከፖሊስ ጋር የታወቀ ግንኙነት የመፍጠርና የሪፖርት ሥርዓት በመዘርጋት ተግባራዊነቱን መከታተል፡በክልል ደረጃ አንድ ወጥ ሥርዓት እንዲኖር ያደርጋል፡

5. በክልሉ የሚያልፉ ዋና ዋና መንገዶችን በምንም መልኩ በታጠቀ ደሁን ባልታጠቀ ዘረፋ እንቅስቃሴን የማወክ ተግባራት እንዳይፈፀም የፀጥታ ሃይሉን ከገጠሩ የሚሊሻዎ ሃይል ጋር አጣምሮ እርገጠና ጥበቃ ያሳቸዉ መሆኑን ያረጋግጣል፡

6. ህገወጥ የትጥቅ ዝዉዉርና ንግድን ይከታተላል በተገኘበትም ለህግ እንዲቀርብ ያደርጋል፡

7. በክልሉ ዉስጥም ሆነ ከክልል ከልል ሲያገጥሙ የሚችሉ የገላ ግጭቶችን አስቀድሞ በማወቅ ወደ ግጭት ከማምራት አስቀድሞ መፍትሄ መስጠት፡ ከክልል ከልል ሲሆንም ተገናኝቶ ይሠራል፡

8. ፀጥታን በሚመለከት ከክልሉ የፀጥታ ምክር ቤት አቅም በላይ የሚሆን ወይም ተጨማሪ ቅንጅት የሚጠይቅ ሁኔታ ተፈጥሮ ሲገኝ በፈደራል ጉዳዮች ሚኒስቴር አማካኝነት ከፈደራል የፀጥታ ምክር ቤት ጋር አስፈላጊዉን ቅንጅት ያደርጋል፡ አዚህ እንዲመቸም በየጊዜዉ ለስ ከክሉ የፀጥታ ሁኔታ ለፈደራል ጉዳዮች ሚኒስቴር ያሳዉቃል፡፡

9. ፀጥታን በሚመለከት በቅንጅት የወጣዉን እቅድ ብሥራ ከናናሉ መሠረት ተግባራዊ መደረጉን ይገመግማል፡ ዉሳኔ ያስተላልፋል፡፡

10. በተዋረድ ለሚቋቋሙት የፀጥታ ምክር ቤቶች ሥራ አፈጻጸም የሚያስፈልጉ መመሪያዎች ያወጣል፡ በሥራ ላይ መዋላቸዉን ይከታተላል፡

11. በተዋረድ በሚቋቋሙ የጸጥታ ምክር ቤቶች የተከናወኑ የሥራ ሪፖርቶችን ያጸምጣል፡፡

9/ በተዋረድ ለሚቋቋሙ የፀጥታ ምክር ቤቶች

በተዋረድ የሚቋቋሙ የፀጥታ ምክር ቤቶችን አመራር፡አደረጃጀትና አሠራር የሚመለከቱ ጉዳዮች በደንብ ይወሰናል፡፡

ክፍል አራት

ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

10.ደንብ የማዉጣት ሥልጣን

የሥራ አስፈጻሚ ደህን አዋጅ ለማስፈጸም አስፈላጊዉን ደንብ ለማዉጣት ይችላል፡፡

11.አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ

ይህ አዋጅ በሕረር ነጋሪ ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ዕለት ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

ሕረር መጋቢት 1 ቀን 1996

ፋስል አብራሂም

የሕረሪ ሕዝብ ክልል ፕሬዝዳንት